# ውድ የጅማ ዩኒቨርሲቲ አዲስ ገቢ ተማሪዎች እንኳን ወደ ጅማ ዩኒቨርሲቲ በደህና መጣችሁልን!!!

## አካዳሚክ ህግና ደንቦች

### 1. የት/ት ምዝገባ

ማንኛውም ለምዝገባ ብቁ የሆነ ተማሪ በዩኒቨርሲቲው በአካል በመገኘት መመዝገብ ይኖርበታል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሬጅስትራር አስቀድሞ ባወጣው የጊዜ ገደብ ብቻ ምዝገባው ይካሄዳል፡፡ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም እና በምዝገባው ዕለት መድረስ ካልተቻለ ከመደበኛው ሁለት የምዝገባ ቀናት በኋላ በሚሰጠው ሶስተኛ የምዝገባ ቀን ተማሪው ማስረጃውን በማቅረብ በቅጣት ይመዘገባል፡፡
በመደበኛ የምዝገባ ጊዜ እና በተጨማሪ የቅጣት ምዝገባ ጊዜ ያልተመዘገበ ተማሪ ቢያንስ ለአንድ ዓመት ከትምህርት ገበታ ይታገዳል፡፡

### 2. የመታውቂያ ካርድ

ሁሉም በዩኒቨርሲቲው የተመዘገቡ ተማሪዎች ለግላቸው የሆነ ለሌላ ሊዛወር የማይችል ልዩ እና ቋሚ የምዝገባ ቁጥር ያለው የመታወቂያ ካርድ ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ የመታወቂያ ካርድ ተማሪዎች ከዩኒቨርሲቲው የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች እና የዩኒቨርሲቲውን ንብረቶች (አቅርቦቶች) በአግባቡ እንዲገለገሉ ይረዳቸዋል፡፡ ስለዚህም በጥንቃቄ መያዝ ይገባቸዋል፡፡

የተማሪው የመታዉቂያ ቁጥር (የምዝገባ ቁጥር) ከማንኛውም ከተማሪው ጋር ተያያዥነት ካላቸው መዝገቦች ላይ የሚሰፍር ሲሆን ተማሪው የዩኒቨርሲቲውን ማኛውንም ግልጋሎት ማግኘት ሲፈለግ ይህን የመታወቂያ ካርድ እና ቁጥር ማቅረብ ግዴታ ነው፡፡

### 3. የት/ት ክፍል ምርጫ

አዲስ ገቢ ተማሪዎች ጅማ ዩኒቨርሲቲ ደርሰው የሚመርጧቸው ት/ት ክፍሎች ምደባ የሚከናወነው 65% በውጤት፤ 5% ለታዳጊ ክልሎች፤ 5% ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እና 25% ለሴቶች ዕድል በመስጠት ነው፡፡

### 4. በትምህርት ገበታ ላይ ስለመገኘት (Class Attendance)

ተማሪዎች በተመዘገቡባቸው ትምህርቶች ላይ በትምህርት ክፍለ ጊዜ እና ላብራቶሪ ልምምድ ሰዓት የመገኘት ግዴታ አለባቸው፡፡ማንኛውም ተማሪ በአንድ ት/ት (ኮርስ) ከ80% በላይ ት/ቱን ካልተከታተለ ለት/ቱ ማጠቃለያ ፈተና መቀመጥ አይችልም፡፡

### 5. ስለመማር ማስተማር ሂደት

በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ለሚገጥሙ ችግሮች ማንኛውም ተማሪ ሊከተለው የሚገባው ሂደት ፍጹም ሕጋዊ እና ሰላማዊ የሆነ አካሄድ ሊሆን ይገባል፡፡ ማንኛውም ችግር ሲገጥም በመጀመሪያ ከት/ት ክፍል ጀምሮ በየደረጃ ያሉ ሃላፊዎችን በማነጋገር መፍትሔ ካልተገኘ በስተመጨረሻ ለዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራር ጥያቄውን ማቅረብ ይቻላል፡፡ ይህ ሲሆን ግን በምንም ዓይነት መልኩ ትምህርትን አቁሞ ጥያቄ ማቅረብ በፍጹም አይፈቀድም፡፡ በዚህ ሂደትም ተማሪዎች ወደማይፈለግ የኃይል እርምጃ የሚገቡ ከሆነ ከዩኒቨርሲቲው የት/ት መርሐግብር ከአንድ ዓመት ጀምሮ እስከ ፈጽሞ መባረር እርምጃ የሚወሰድባቸው ይሆናል፡፡ የሚቀርቡ ጥያቄዎችም በተቻለ አቅም በዩኒቨርሲቲው በተቋቋመው የተማሪዎች ኅብረት በኩል መሆን ይጠበቅበታል፡፡በተጨማሪ በግቢ ውስጥ ምንም ዓይነት ሃይማኖታዊም ይሁን ፖለቲካዊ አቋም ማንጸባረቅ እና እንቅስቃሴ ማድረግ አይቻልም፡፡ ዩኒቨርሲቲው የሚከተለው Secular የሆነ የአካዳሚክ ሥርዓት በመሆኑ ተማሪዎች ሕጉን ጠንቅቀው አውቀው እንዲተዳደሩበት ይጠበቃል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ማንኛውም ተማሪ በተለይ ብሔርን ወይም ሃይማኖትን መሠረት ያደረገ ግጭት ብፈጥር ሙሉ በሙሉ ከዩኒቨርሲቲው የት/ት መርሐግብር የሚሰናበት እና በወንጀልም በሕግ ፊት የሚጠየቅ ይሆናል፡፡

### 6. የፈተና ሕግ (Exam Rule)

ተማሪዎች ለፈተና ሲቀመጡ እራሳቸውን ችለው መሥራት ይገባቸዋል፡፡ ማለትም ማንኛውም የትምህርት መርጃ መሣሪያ ይዞ መግባት፤ መቀያየር፤ ማውራት፣ መኮረጅ፣ ማስኮረጅ፣ በሞባይል እና ሌሎች መሰል የቴክኖሎጂ ውጤቶች መልስ መቀበልም ሆነ ማስተላለፍ በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡ የትምህርት ሂደቱን የሚረብሹ እና ተአማኒነት የሌላቸው፤ በሚኮርጁና በሚያጭበረብሩ በአጠቃላዩ የሌላውን የሥራ ውጤት እንደራሳቸው አድርገው በሚያቀርቡ ተማሪዎች ላይ ዩኒቨርሲቲው ጥብቅ የሆነ የሥነ ምግባር እርምጃ ይወስዳል፡፡
ማንኛውም ተማሪ ሲኮርጅ ወይም ሲያስኮርጅ እጅ ከፍንጅ ከተያዘ በቴስት ፈተናዎች ከሆነ ውጤቱ ዜሮ ሲሆን የማጠቃለያ ፈተና ከሆነ ደግሞ ሙሉ የኮርሱ ውጤት ተሰርዞ "F" ይሆናል፡፡ ማንኛውም ተማሪ ለሁለተኛ ጊዜ ሲኮርጅ ወይም ሲያስኮርጅ ከተያዘ ከዩኒቨርሲቲው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይባረራል፡፡ በኩረጃ ወንጀሎች ምክንያት “F” በመጡ ኮርሶች ላይ የማካካሻ ፈተና (Make up exam) መውሰድ አይቻልም፡፡

## 7. ማካካሻፈተና (Make up exam)

የማካካሻ ፈተና የሚሰጣቸው ተማሪዎች የወሰነ ትምህርቱን ያጠናቀቁና ፈተና ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ያመለጣቸው ለዚህም በቂ የሆነ ማስረጃ ሲኖራቸው ነው፡፡ በቂ ከሆኑ ማስረጃዎች መካከል የጤና እክል፤ በሐኪም ማስረጃ የተረጋገጠ የቤተሰብ አባል በሞት መለየት፤ ሴቶች በወሊድ ጊዜ፤ያለጥፋት በህግ ቁጥጥር ስር መዋል ወዘተ ናቸው፡፡ ማንኛውም የማካካሻ ፈተና የሚሰጠው ቀጣይ ሴሜስተር ምዝገባ በተፈጸመ ሁለት ሳምንታት ግዜ ውስጥ ነው፡፡አንድ ተማሪ በዩኒቨርሲቲው ቆይታው ከሁለት ጊዜ በላይ የማካካሻ ፈተና አይፈቀድለትም፡፡ አራትና ከዚያ በላይ በሆኑ ትምህርቶች የማጠቃለያ ፈተና ያመለጠው ተማሪ ትምህርቱን በማቋረጥ በቀጣይ ዓመት መጥቶ ለኮርሶቹ ተመዝግቦ ትምህርቱን መቀጠል ይጠበቅበታል፡፡

## 8. የአንደኛ ዓመት ተማሪዎች በአንደኛ ሴሜስተር የሚጠበቅባቸው የትምህርት ደረጃ ውጤት

| የሴሚስተር ውጤት (SGPA) | አማካይ ውጤት (CGPA) | ደረጃ (Status) |
|---|---|---|
| <1.25 | <1.25 | **Academic Dismissal (AD)** |
| 1.25 – 1.49 | 1.25 – 1.49 | **Academic Dismisal for Readmission (ADR)** |
| 1.5 – 1.74 | 1.5 – 1.74 | **Warning** |
| >1.74 | >1.74 | **Pass** |

## 9. ውጤት በተመለከተ ቅሬታ ስለማቅረብ

ማንኛውም ተማሪ በዩኒቨርሲቲ ሕግና ደንብ መሰረት በውጤቱ ላይ ቅሬታ ማስማት ይችላል፡፡ ነገር ግን አንድ ተማሪ ቅሬታ ማስገባት የሚችለው በቀጣዩ ወሰነ ትምህርት በተጀመረ በአስር ተከታታይ ሥራ ቀናት ውስጥ መሆን አለበት፡፡ ማንኛውም ቅሬታ ከተፈቀደለት 10 ቀናት ውጭ ቅሬታው ቢቀርብ አይስተናገድም፡፡ ማንኛውም ተማሪ የተሰጠው የመጨረሻ ውጤት ትክክለኛ ያልሆነ፣ የተጭበረበረ፣ ግምታዊ እና ህጋዊ ያልሆነ የምዘና ዘዴ ነው ብሎ የሚያምን ከሆነ በመጀመሪያ ደረጃ ችግሩን ለአካዳሚክ አማካሪው/ለት/ት ክፍሉ ኃላፊ ያመለከታል፡፡ መምህሩ ለተማሪው የፈተና ውጤቱን እና ሥራውን ማሳየት ይጠበቅበታል፡፡ አካዳሚክ አማካሪውና የትምህርት ክፍሉ ሃላፊ በመወያየት መምህሩ ለተማሪው የፈተና ውጤቱን እንዲመረምር እና ስህተትም ከሆነ እንዲያስተካክልለት ያደርጋሉ፡፡ ስህተት ተፈጽሞ መምህሩ ለማስተካከል ፍቃደኛ ካልሆነ ግን በት/ት ክፍሉ ጉባዔ በሚወከል ኮሚቴ ፈተናው እንደገና ታርሞ ውጤቱ እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡ ተማሪው ግን በማወቅ ያለመምህሩ ጥፋት ውጤቴ ይስተካከልልኝ በማለት ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ሲሞክር ቢገኝ ግን የሙሉ ኮርሱን ውጤት ዜሮ እስከሚያደርግ እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፡፡

## 10. የቤተመጻሕፍት አጠቃቀም

በዩኒቨርሲቲው ለሴሜስተሩ ት/ት ምዝገባ ፈጽሞ የሚገኝ ተማሪ ሁሉ የዩኒቨርሲቲውን አብያተ መጻሕፍት መጠቀም ይችላል፡፡ አገልግሎቱን ለማግኘት ማንኛውም ተማሪ የታደሰ የተማሪነት መታወቂያ ይዞ መገኘት አለበት፡፡ በቤተመጻሕፍት ውስጥ ከጓደኛ ጋር ማውራት፤ የስልክ ጥሪ ድምጽ ማሰማት፤ የኮቴ ድምጽ ያለውን ጫማ አድርጎ መግባት እና የመኝታ ልብሶችን በመልበስ ለመግባት መሞከር በፍጹም የተከለከለ ነው፡፡ የተዋሱት መጽሐፍ ላይ መጻፍ፤ ገጾችን መቅደድ እና መጽሐፉን ያለፍቃድ ከቤተመጽሐፉ ውጪ ይዞ ለመውጣት መሞከር ከአንድ ዓመት እስከ አጠቃላይ መባረር እርምጃ ያስወስዳል፡፡ በበቂ ቁጥር የሚገኙ መጻሕፍት በውስት ማግኘት የሚቻል ሲሆን በአገልግሎትም ቤተመጻሕፍቱ እስከ 24 ሰዓት አገልግሎትየሚሰጥ ነው፡፡

## 11. በዩኒቨርሲቲ የሚገኙ ንብረቶች አጠቃቀም

ማንኛውም ተማሪ በዩኒቨርሲቲው የሚገኙ እና የሚገለገልባቸውን ንብረቶች በጥንቃቄ እና በአግባቡ ሊይዛቸው ይገባል፡፡ በንብረቶቹ ላይ ጉዳት ቢያደርስ ንብረቶቹን እንዲተካ ከመደረጉም በላይ በፈጸመው ጥፋት ከዩኒቨርሲቲው የት/ት መርሐግብር ለመጨረሻ ግዜ ሊሰናበት ይችላል፡፡

## 12. ከዩኒቨርሲቲው መባረርን የሚያስከትሉ ጥፋቶች፡-

ከላይ በዝርዝር ለማቅረብ እንደተሞከረው ከብዙው በጥቂቱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ጥፋቶችን የፈጸመ ተማሪ ከዩኒቨርሲቲው የት/ት መርሐግብር ለመጨረሻ ግዜ ይባረራል፡

ሀ. በዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች መካከል ግጭት ለመፍጠር የሞከረ ወይም በግጭቱ ተሳታፊ የሆነ/ች

ለ. በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ድምጽ ባለው ወይም በሌለው መሳሪያ ጉዳት ያደረሰ/ች፣

ሐ. በዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ ላይ የድብደባ ሙከራ ያደረገ/ች እና የፈፀመ/የፈፀመች

መ. የአስገድዶ መድፈር ወንጀል የፈጸመ/ች

ሠ. የተጭበረበረ የትምህርት ማስረጃ አቅርቦ ተመዝግቦ የተገኘ/ች/፣

ረ. ተገቢውን ክፍያ ሳይፈጽም ወይም የወጪ መጋራት ሳይፈርም የአገልግሎት ተጠቃሚ ሆኖ የተገኘ/ች/፣

# መልካም የትምህርት ዘመን!



**የጅማ ዩኒቨርሲቲ ሬጅስትራር ጽ/ቤት**